# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 46 ኛ ሳምንት

## አቡነ ተክለይማኖት ጻድቅ

**ዓላማ፡-**

- የአቡነ ተክለሃይማኖትን ሕይወትና መልካም ሥራዎች በመማር አሠረ ፍኖታቸውን መከተል

**ምንባብ፡-**

- ገድለ ተክለሃይማኖት፣ስንክሳር

**ጥቅስ**

- *"ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ዉኃ ብቻ በደቀመዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም፡፡"*ማቴ.10÷42

**መግቢያ፡-**

- ቅዱስ፣ጻድቅ ብለን የምናከብራቸው የቅድስናን ሕይወት የኖሩ፣ራሳቸውን ለጸሎት እና እግዚአብሔርን ለማገልገል የሠጡትን ነው፡፡
- በዛሬው ትምህርታችን በኢትዮጵያ ከነበሩት ትላልቅ ቅዱሳን አንዱ ስለሆኑት እንማራለን፡፡ ከትምህርቱ በኋላ በቤተክርስቲያን የቅዱሱን ሥዕል ፈልጉ፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1. ሐዋርያት ለምን ለ14 ቀናት ጾሙ?

    ________________________________________

2. እመቤታችን መቼ አረገች?

    ________________________________________

3. እርገትዋን በመጀመሪያ ያየው ሐዋርያ ማነው?

    ________________________________________

**ትምህርቱ፡-**

- ተክለሃይማኖት የተባሉ ጻድቅ በኢትዮጵያ ነበሩ፡፡ እግዚአብሔርን ከሚወዱ ቤተሰቦች የተወለደ ሲሆን÷በየወሩ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል እያከበሩ ነዳያንን ይመግቡ ነበር፡፡ ጻድቅ ተክለሃይማኖትም የቤተሰቦቹን አሠረ ፍኖት ተከተለ፡፡ ቤተሰቦቹ ወደ እግዚአብሔር ሲሄዱ(በሞተ ሥጋ ሲያርፉ)፣ያለውን በሙሉ ለድሆች መጽውቶ÷ስለ ክርስቶስ ለማስተማር ራሱን ለየ፡፡
- ስለ ክርስትና በማስተማር ብዙ ሕዝቦችን እያጠመቀ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተዘዋውሯል፡፡ ለረጅም ሰዓታትም ይጸልይ ነበር፡፡ በአንድ እግሩ ብቻ ቆሞ በመጸለይም አንድ እግራቸውን እስከማጣት ደርሠዋል፡፡
- ጻድቁ በተራራ ላይ በምትገኝ ገዳም ሲኖሩ÷ በገመድ እየወጡና እየወረዱ ይኖሩ ነበር፡፡ ታዲያ አንድ ቀን እየወረዱ በድንገት ገመዱ ተበጠሰ፡፡ ጻድቁ ተክለሃይማኖት ጸለዩ፣ እግዚአብሔርም ስድስት ክንፍ ሰጣቸው፡፡ ከተራራው በተዓምራት በክንፋቸው እንደመላእክት ወረዱ፡፡
- የትም ሲሄዱ የታወሩ፣ሽባ የሆኑና በተለያዩ በሽታዎች የተያዙ ወደ እርሱ እየመጡ ይፈወሱ ነበር፡፡ ሁሉንም ያድናቸው ስለክርስቶስ እየመሠከረም ክርስቲያን ያደርጋቸዋል፡፡ የቅዱስ ሚካኤልን ቀን እንደቤተሰባቸው ያከብራል፡፡ ቅዱስ ሚካኤልም ይረዳቸው ነበር፡፡
- ጻድቁ ተክለሃይማኖት ድሆችን የሚረዱ፣ሕሙማንን የሚፈውሱ፣ስለክርስቶስ የሰበኩ እና በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ብዙ ሰዎች ያጠመቁ ቅዱስ ናቸው፡፡
- 99 ዓመት ሲሞላቸውም ታመሙ፡፡ መነኮሳቱን ሰብስቦ የጸሎትና የፍቅር አገልግሎታቸውን እንዲቀጥሉ አሳስበዋቸው፡፡ **ነሐሴ** 24 በክብር አረፉ፡፡
- ጸሎታቸውና ቃልኪዳናቸው ከሁላችንም ጋር ይሁን አሜን፡፡

**መዝሙር**

አማን በአማን(4)<br>
ተክለሃይማኖት ፀሐይ

**ይቆየን፡፡**